የአደም ልጅ ሁለት በገንዘብ የሞላ ሸለቆ ቢኖረው ኖሮ ሶስተኛ ሸለቆ ይመኛል።

አነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል: «የአላህ መልክተኛ -የአላህ ሰላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ብለዋል፦ "የአደም ልጅ ሁለት በገንዘብ የሞላ ሸለቆ ቢኖረው ኖሮ ሶስተኛ ሸለቆ ይመኛል። የአደምን ልጅ ሆድ ከአፈር በቀር የሚሞላው የለም። ወደ አላህ ተፀፅቶ በተመለሰ ሰው ላይም አላህ ተውበቱን ይቀበለዋል።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - የአደም ልጅ በወርቅ የሞላ ሸለቆ ቢኖረው ኖሮ በተፈጥሮው ካለው ስግብግብነት አንፃር ሌሎች ሁለት ሸለቆዎችን ይመኝ ነበር። የአደም ልጅ ሙቶ ከርሱ በቀብሩ አፈር ካልሞላ በቀር ለዱንያ ስግብግብ ከመሆን አይወገድም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4963